28 05 2022

**ውታፍ ነቃይ**

ከጣሰው እንደልቡ

ከሁለት ሳምንት በፊት ባቀረብሁት ጽሁፍ አዶልፍ ሂትለርን "ስጋ ለብሶ የተገለጸ ሰይጣን ነው" የሚሉ የታወቁ ሊሂቃን እንዳሉና አብይ አህመድ አሊ ደግሞ አዶልፍ ሂትለርን የሚያስንቅ ሰይጣን መሆኑን ጠቅሼ ነበር፡፡ ዛሬ የራሱን የአብይ አህመድ አሊን "እርካብና መንበር" የሚለውን መጽሀፍ ዋቢ አድርጌ ለመረዳቴ ማጠናከሪያ ለማቅረብ ልሞክር፡፡

አብይ አህመድ አሊ "እርካብና መንበር" በሚለው መጽሀፉ በገጽ 36 ላይ፣ ስልጣን ስለያዘ መሪ ሲገልጽ፣ "መስፍኑ የተለበጠ ማንነት ሊኖረው ይገባል፣ ሰዎች የሚያውቁት የላዩን ብቻ ሲሆን አስፈላጊ የሆነ ጊዜ ሁለተኛውን ድብቁን ማንነቱን ይገለጻል፡፡ በሰላሙ ጊዜ ደስ የሚያሰኛቸውን ነገር በማድረግ በህዝብ ልቦና ውስጥ ተደላድሎ መቀመጥ ይቻላል፡፡ ታዲያ የአመጽና የመከዳት ምልክት በታዬ ጊዜ በሁለተኛው በተለበጠ መልክ መገለጽ ተገቢ ነው፡፡ በፍቅር ጊዜ መልአክ በአመጽ ጊዜ ሰይጣን ሊሆን እንደሚቻል ማሳወቅ አለበት፡፡" ይለናል፡፡ ይህ ማለት ሰይጣንነቱን እኔ ሳልሆን እራሱ አምኖ የመሰከረው ማንነቱ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህም ተጨማሪ በቅርብ ጊዜ ስለሚፈጸሙ መንግስት መር ስለሆኑ ጭፍጨፋዎች በጣም ጥቂቱን መጥቀስ ከበቂ በላይ ሰይጣንነቱን የሚያሳብቅበት ይመስለኛል፡፡

ፋኖንና ዐማራን ለማንበርከክ በእግረኛ፣ በሄሊኮፕተርና በድሮን የታገዘ ሙሉ መንግስታዊ ጦርነት በህዝብ ላይ ከፍቷል፡፡ "ሰይጣን ከሀጢያት ጋር ያብራል" እንደሚባለው፣ የአብይ አህመድ ጦር - ሰው የሚያርደውንና የሚያፈናቅለውን "ኦነግ ሸኔን" በመከላከያ ስም የአማራን ልዩ ኃይል ልብስ ለብሶ በአማራ ክልል በመግባት እንዲገል ሙሉ መንግስታዊ ትብብር እያደረገለት መሆኑ እናያለን፡፡

የሚጮህለት ያጣው የሲዳማ ክልል፣ በኦነግ ኃይል የሲዳማዎች ቤት በእሳት እዬነደደና ከብቶቹም እየተዘረፉበት ነው፡፡አዋሳም ከደቡብ ህብረት ከወጣች በኋላ እድገት እርቋት ተራቁታለች፡፡

ጋዜጠኞችና የህብረተሰብ አንቂዎች በገፍ እየታፈኑና እየታሰሩ ሲሆን፣ በአዲስ አበባና አካባቢው በሚኖሩ አማሮች ላይ የተጀመረው አፈናና መዋከብ ከቀን ወደ ቀን እዬጨመረ ሄዷል፡፡

ሰይጣንን አስመልክቶ፣ "መልካም የሆነውን ሁሉ እዬተቃወመ የራሱን መንግስት ሊያቆም ይጥራል" እንዳለው መጽሀፍ ቅዱስ፣ ኦነጎች በኢትዮጵያ መቃብር ላይ ኦሮሚያን እንፈጥራለን ብለው በፎከሩት መሰረት፣ ትናት አብይ ወደ አማራ ክልል መርቶና ጎትቶ ባመጣው የወያኔ ጦር፣ እሱንም ተከትሎ በተፈጸመው ሰቅጣጭ ወንጀሎች፣ ዛሬ የአማራና የትግሬ ህዝብ በቀላሉ የአንድ ሀገር ህዝብነት መንፈስ የሚያሻክር ስሜት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ያም የሆነው፣ በአብይ አህመድ ትእዛዝ የመከላከያ ሰራዊት መሳሪያውንና ምሽጉን እዬለቀቀ ለትግራይ አማጺያን እንዲለቅ በተደረገ የታቀደ ሴራ ነው፡፡ ይህ የሆነው በትናቱ ከትግራይ ጋር በነበረው ጦርነት ሲሆን፣ ዛሬ ደግሞ፣ የአማራን ክልል ልዩ ሃይል ልብስ አልብሶ ከኦሮሚያ ክልል ባመጣው የኦሮሚያ ልዩ ኃይል በአማራ ክልል ህዝብ ላይ ጦርነት ከፍቷል፡፡ በዚህ ጦርነት አማረኛ መናገር የማይችሉ ገዳዮችን አሰማርቶ የአማራን ህዝብ ከኦሮሞኛ ተናጋሪው ህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ የማድረግ ሴራ ላይ ተጠምዷል፡፡ ይህ በአብይ አህመድ ቃል፣ የተለበጠው ሁለተኛ መልኩ ወይም ሰይጣናዊ መልኩ መሆኑ ነው፡፡ ማቲዎስ ወንጌል 25፣14 ሰይጣንን "የመልካም ነገር ተቃራኒ" የሚለው፣ እንዲህ አይነቱን ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን፣ ከደግነት ይልቅ ክፋትን፣ ከአንድነት ይልቅ መለያዬትን የሚያራምድ የአብይ አህመድ አሊን አይነቱን ነው፡፡

አንድም ወታደር አልተማረከብኝም ሲል የነበረው የአብይ አህመድ አስተዳደር፣ ከደብረ ጽዮን ጋር ባደረገው ስምምነት ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑ ኦሮሞኛ ተናጋሪ ምርኮኛ፣ ከትግራይ አምጥቶ በወልድያ መስመር ላይ በማሰማራት ሳይውሉ ሳያድሩ በአማራ ሚሊሺያ፣ ልዩ ኃይልና ፋኖ ላይ ትንኮሳና ጥቃት ፈጽመዋል፡፡ ባጠቃላይ የኦሮሙማው የዐቢይ አሕመድ መንግሥት በዐማራ ክልል በጎጃም፣ በወልድያ ሰሜን ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በሲዳማ ከሲዳማ ጋር ጦርነት ከፍቷል፡፡ ውታፍ ነቃዩም በእጥፍ ወደ ስራ ተሰማርቶ የአብይ አህመድን ድርጊት ህጋዊነትና ወንጀሉን ለማስተባበል የሶሺያል ሜዲያውን አጨናንቆታል፡፡ መሬት ላይ የሚታዬው ሀቁ ግን በመንግስታዊ ሽብርተኝነት ሀገራችን እርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መሆኑዋ ነው፡፡ የኦነግ ብሄረተኞች እንደፎከሩት በኢትዮጵያ መቃብር ላይ ኦሮሚያ የሚባል ሀገር ለመፍጠር መሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡ ፋኖንና ዐማራን ለማንበርከክም፣ ከኦሮሚያ ወደ ዐማራ ክልል የመከላከያና የዐማራ ልዩ ኃይልን ልብስ አልብሶ የላከው የኦነግ ሰራዊት በናዝሬት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውርደው የኦነግን ባንዲራ ሲሰቅሉና ነፍጠኛ በሌላ ስሙ አማራ ሀገራችንን ለቆ ይውጣ ሲሉ ሰምተን ታዝበናል፡፡ አማራ ክልል ላይ የተጀመረው ማፈንና መሰወር ዛሬ አዲስ አበባ ላይ በአማራ ህዝብ ላይ እዬተፈጸመ ነው፡፡

በፋኖና በአማራ ህዝብ ገዢ ሀሳብና መመሪያ ሆኖ የተያዘው "ባልጀራህን እንደራስህ ውደድ" በሚል ትምህርት ላይ የተገነባ የሞራል ልእልና ትምህርት፣ የህልውና አደጋ ላለበት ህዝብ ፋይዳ እንደሌለው ማኪያቬሊ "ባልጀራህን እንደራስህ ውድድ" የሚለው የሃይማኖት ትምህርት በፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነትና በመሳሪያ ሃይል ካልታገዘ ዋጋቢስ መሆኑን ያስተምረናል፡፡ በአብይ አህመድ የተዘመተበት የአማራ ህዝብ ደግሞ ይዋል ይደር እንጂ መንግስት እራሱ አሳዳጁና ገዳዩ መሆኑን እየተረዳው ሲመጣ አሁን ያለውን ወታደራዊ  ትጥቁንና ድርጅቱን ከፖለቲካ ድርጅት ጋር ማቀናጀትና ለስልጣን ባለቤትነት መታገል ወዶም ሳይሆን ተገፍቶ የሚደርስበት እርከን መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

ሲጀመር ብአዴን የሚሉት ድርጅት መለስ ዜናዊ በአማራው ህዝብ ከላይ የጫነበት እንጂ የአማራ ህዝብ የወከለው፣ ለአማራ ህዝብ የቆመ ድርጅት አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ ዛሬ በዐብይ አሕመድ አሊና በትግሬው መከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ፣ በብርሃኑ ጁላና የእነሱ ተላላኪ በሆኑ ብአዴኖች፣ እንደነ ጀኔራል አበባው ታደሰ፣ ተመስገን ጥሩነህ፣ ሰማ ጥሩነህና፣ ይልቃል ከፋለ የሚመራውና የአማራን ልዩ ኃይል ዩኒፎርም የለበሰው ከኦሮሚያ ክልል የመጣው ለጊዜውም ቢሆን ህዝብን ማደናገር ይችላል፣ ግን ዘላቂነት አይኖረውም፡፡ ትናት በሞጣ የተጨፈጨፉ ወጣቶችን ማን እንደገደላቸው ሚሊዮን ውታፍ ነቃይ በሶሺያል ሜዲያው ቢዘምት ሊያስተባብለው አይችልም፡፡ አብይ አህመድ አሊ፣ ሰሎሞን ሹምዬን፣ መስከረም አበራን፣ አቶ ታዲዎስ ታንቱንና ሌሎችንም እያፈነና እያሰረ፣ "ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያ!" ብሎ ጿድቅ መስሎ መቅረብ፣ ያራዳ ልጅ እንደሚለው "የተበላበት እቁብ" ሆኖዋል፡፡ ኦሮሞኛ ተናጋሪ ሆኖ የዐማራ ልዩ ኃይል ልብስ ለብሶ በሰሎሞን ኢታና የሚታዘዘው የመከላከያ ሰራዊት በወልድያና በምሥራቅ ዐማራ ፋኖዎች ላይ ተኩስ ከፍቶ ሰላማዊ ሰዎችን እዬገደለ ያለውን የኦነግ ሰራዊት "ሰላም አስጠባቂ ነው" ብትለው "ሞኝህን ፈልግ" የሚል ህዝብ ተፈጥሮ በአደባባይ "አብይ አህመድ ለፍርድ ይቅረብ" የሚል ሰልፍ በቪዲዮ መረጃውን እያዬን ነው፡፡

"በፍቅር ጊዜ መልአክ በአመጽ ጊዜ ሰይጣን የሆነ የተለበጠ ሁለት መልክ ይኑርህ" የሚለው የአብይ አህመድ አሊ አስተምህሮ ቢያንስ ውታፍ ነቃይ ያልሆነና ለህሌናው አዳሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ እንዳለ የረሳ ይመስላል፡፡ እዚህ ላይ አይሁዳዊው ጋዜጠኛ ቲዎዶር ሄርሚዝን ያስታውሰኛል፡፡

ሀንጋሪ ተወልዶ ቬዬና ውስጥ ይኖር የነበረው አይሁዳዊ ጋዜጠኛ ቲዎዶር ሄርሚዝ፣ አንድ ድሬ ይፊውስ የተባለ አይሁዳዊ የፈረንሳይ የጦር መኮንን፣ የሀገሪቱን ወታደራዊ ሚስጢር ለጀርመን አሳልፈህ ሰጠህል ተብሎ በሀሰት ተከሰሰ፡፡ ቲዎዶር ሄርሚዝ በድሬ ይፊውስ ላይ በሚደረገው መንገላታት ስሜቱ

ክፉኛ ተነክቶ “አይሁዳውያን የራሳቸውን ሀገርና መንግስት ካላቋቋሙ በስተቀር ለህልውናቸው ምንም ዋስትና የላቸውም” ሲል በጋዜጣ ጻፈ፣ እንዲሁም የጽዮናውያንን ጉባኤ በመጥራትና ሌሎችንም በማስተባበር ለዚህ አላማ መታገል ጀመረ፡፡ ይህ ትግልም ውሎ - አድሮ ዛሬ ኢስራኤል የምትባለዋን ሀገር ለመፍጠር ቻለ፡፡ እዚህ ላይ መጥቀስ የፈለግሁት፣ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰው የአማራው ህዝብ ህልውና አደጋ፣ እንደ ቲዎዶር ሄርሚዝ ስሜታቸው ክፉኛ የቆሰለ ግለሰቦችም ሆኑ ስብስቦች እየተጠናከሩና እለት በእለት ወደ አንድነት እየተቀራረቡ እየመጡ መሆኑን “ጻድቅና ሰይጣን የሆነ ሁለት መልክ ይኑርህ” የሚለው አብይ አህመድና ውታፍ ነቃይ ተከታዮቹ ያስተዋሉት አይመስለኝም፡፡ የአማራ ህልውና እያሳሰበውና በአማራው ህዝብ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ ስሜቱን እያቆሰለው ለፍልሚያ የሚነሳው የአማራ ህዝብ በየጊዜውና በእየቀኑ እየጨመረ ወደ ጥንቱ ሊመለስ ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ እነዚህ አስመሳይ ኢትዮጵያውያንና ውታፍ ነቃዩች አሻግረው ማዬት አቅቷቸው ጊዜያዊ መከፋፈልን እንደመከራከሪያ የሚያቀርቡ ከሆነ፣ በአይሁዳውያን መካከልም ሙሉ ለሙሉ አንድ አይነት አመለካከት አልነበረም፡፡ ከፍልስጤምና ከአረብ ህዝቦች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት አስመልክቶ የተለያዩ አመለካከት የነበራቸው ነበሩ፣ የአይሁድን ህልውና በተመለከ ግን ልክ እንደ ዛሬው በአማራ ህዝብ ዙሪያ እንደተሰባሰቡ ስብስቦች አንድ አይነት መግባባት ላይ ደርሰው ነበር፡፡ የሚፈለገውም ያ ነበር፡፡

ራእይ 12፥10 ሰይጣንን “የወንድሞቹ ከሳሽ” እንደሚለው፣ አብይ አህመድ አሊ እሱ ሁለተኛ መልክ በሚለው በሰይጣናዊ መልኩ ተገልጾ፣ ለአማራ ህዝብ ከዚያም አልፎ ለኢትዮጵያ ህዝብ ወንድምና መከታ የሆነውን ፋኖን ከሷል፡፡ “እኛም ነቅተናል ጉድጓድ ምሰናል” እንዳለቸው፣ የኢትዮጵያ ህዝብም የሰይጣኑን የአብይ አህመድን ሁለተኛውን መልክ አይቶ ነቅቷል እላለሁ፡፡

መጽሀፉን ማንበብ የሚፈልግ በዚሁ በኢትዮ ፓትርዮት ድህረገጽ ማግኘት ይችላል፡፡